

: amharisk

Informasjon til enslige mindreårige asylsøkere

NOAS

ያለ ወላጅ ወይም ያለ አሳዳጊ ጥገኝነት ለሚጠይቁ ለአካለ-መጠን ላልደረሱ ልጆች የሚሰጥ ማብራርያ

ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 18 ዓመት ለሆናቸው ልጆች

ከ18 ዓመት በታች ነህ/ነሽ? ወደ ኖርዌይ የመጣኸው/የመጣሽው ያለ ወላጆች ወይም ያለ ተንከባካቢ ነው? ጥገኝነት ጠይቀሃል/ሻል? ይህ ከሆነ የምትጠራው/የምትጠሪው ለአቅመ-አዳም ያልደረሰ ብቸኛ ጥገኝነት ጠያቂ ተብለህ/ተብለሽ ነው።

በዚህ በራሪ ወረቀት ውስጥ አንድ ብቸኛ ለአቅመ-አዳም ያልደረሰ ጥገኝነት ጠያቂ ሰው፣ በኖርዌይ የጥገኝነት ከለላ ጥያቄ በሚያቀርብበት/በምታቀርብበት ወቅት ሊኖርህ/ሊኖርሽ ስለሚችለው መብትና ግዴታ ለማሳወቅ እንዲያስችል ሆኖ የተዘጋጀ የመረጃ በራሪ ወረቀት ነው።

በትውልድ አገርዎ ስላሉት ቤተሰቦችዎ:

ስለቤተሰቦችዎ ሁኔታ መናገር እጅግ አስፈላጊ ነው። UDI ቤተሰብዎ የት እንዳሉ ካላወቀ፣ ሊያስፈልጋቸው ይችላል።ስለሆነም ቤተሰቦችዎ የት እንደሚኖሩ መንገርዎ አስፈላጊ ነው

ስለቤተሰብህ እና ቤተሰብህ የት እንዳሉ ለኖርወይ ስደተኞች አስተዳደር መናገር አስፈላጊ ነው::

የኖርወይ ስደተኞች አስተዳደር ቤተሰብህን ሊፈልግ ይችላል::

1. የጥገኝነት ከለላ መብት ያለው ማን ነው?

- አንድ ሰው ለመገደል፣ ለሰቆቃዊ ግርፋት፣ ወይም ለሌላ አደገኛ ጥቃቶች የተጋለጠ ሆኖ ወደ ትውልድ ሀገሩ ቢመለስ በነኝህ አደገኛ ሁኔታዎች ውስጥ ሊወድቅ ይችላል ተብሎ ከታመነበት ጥገኝነት የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው።

- የአገርዎ መንግሥት ለደህንነትዎ ጥበቃ ሊያደርግልዎት የሚችል ከሆነ ወይም በትውልድ አገርዎ በሌላ የመኖርያ ሥፍራ ለአደጋ የማይጋለጡ ከሆነ በተለመደው አሠራር በኖርዌይ ውስጥ የጥገኝነት ከለላ የማግኘት መብትአይኖርዎትም።

- ያለ ወላጅ እና ጠባቂ በኖርዌይ የጥገኝነት ከለላ የሚጠይቁ ለአቅመ-አዳም ያልደረሱ ብቸኛ ስደተኞች፣ ጉዳያቸው ከአዋቂ ሰዎች መስፈርት በታች ለዘብ ባለ ሁኔታ እንዲታይ ይደረጋል።

- ትክክለኛ የጥገኝነት ከለላ መብት ሊኖረው የሚችለው ማን ነው የሚለውን ጥያቄ የሚወሰነው፣ ኖርዌይ በተፈራረመችው የአለም አቀፍ ስምምነቶች ነው።

2. በሰብአዊ ርህራሄ ድንጋጌ መሥፈርት መሰረት የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጠው የሚችለው ማን ነው?

- ለጥገኝነት ከለላ፣ መስፈርቱን የማያሟሉ ከሆነ፣ መንግሥት ጉዳይዎትን ገምግሞ በጽኑ የሰብአዊነት አመለካከት አዘኔታ መስፈርት መሠረት፣ ወይም ከኖርዌይ ጋር ባለዎት ልዩ ቁርኝት ወይም ትሥሥር፣ የመኖርያ ፈቃድ ሊያገኙ የሚችሉበትን መንገድ መንግሥት ታሳቢ ውስጥ ያስገባል ወይም ይመረምራል።

3. የተገደበ የመኖሪያ ፈቃድ የሚያገኘው ማነው?

- በኖርዌይ ወስጥ ፈቃድ ሊያሰጣችሁ የሚችለው ብቸኛው ምክንያት፣ወደ ትውልድ አገርዎ ቢመለሱ በቂ እንክብካቤ ሊያደርግልዎ የሚችልን ግለሰብ ይኑር፣ አይኑር UDI ስላላረጋገጠ፣ የተገደበ የመኖርያ ፈቃድ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ ደግሞ ተግባራዊ የሚሆነው፣ UDI ማመልከቻዎትን እየመረመረ ባለበት ወቅት እድሜዎ ከ16 ዓመት በላይ ከሆነ ነው።

- ይህ የተገደበው የመኖሪያ ፈቃድ የሚጸናው እድሜዎ 18 ዓመት እስኪሞላ ድረስ ነው።

- ይህ የተገደበ የመኖርያ ፈቃድ ሊታደስ አይችልም እንዲሁም ቤተሰብዎ ወደ ኖርዌይ የመምጣት መብት የለውም።

4. የጥገኝነት ማመልከቻዎትን የሚመለከተው የትኛው አገር ነው?

- በኖርዌይይ ውስጥ የጥገኝነት ጥያቄ የጠየቀ ሁሉ፣ ጥያቄው በኖርዌይ ውስጥ ይታይለታል ማለት አይደለም። የዳብሊን ሕግ በአውሮፓ አገራት መካከል የተፈረመ የትብብር ስምምነት ሲሆን ይህ ማለት ደግሞ የጥገኝነት ከለላ ማመልከቻ ያቀረበ ሰው ጉዳዩ ሊታይለት የሚችለው በስምምነቱ ውስጥ ከተካተቱ ሃገራት ውስጥ በአንዱ አገር ብቻ ነው።

- ወደ ኖርዌይ ከመምጣትዎ በፊት በአንዱ ሌላ የአውሮፓ አገራት ውስጥ ለጥገኝነት ከለላ አመልክተው ከሆነ ወይም ወላጆችዎ አለበለዚያም ሌሎች የወላጅነት ሃላፊነት የወሰዱ ሰዎች በዚያ አገር ውስጥ ካሉ፣ የኖርዌይ መንግሥት ጉዳዩ እንዲታይ እርስዎን ወደ ተባለው አገር ያስተላልፍዎታል።

- የስደተኝነት ከለላ ጥያቄ በአውሮፓ አገራት በአንዱ ውስጥ ጠይቀው እንደሆነ ለማረጋገጥ የኖርዌይ መንግሥት የጣት አሻራዎትን ይመረምራል።

- የኖርዌይ መንግሥት ወደ አንዱ የአውሮፓ አገራት እንዲወጡ ካደረገዎት፣ ይግባኝ ማለት መብትዎ የተጠበቀ ስለሆነ ጠበቃዎ በዚህ ላይ ሊረዳዎት ይችላል።
- በአንዱ የአውሮፓ አገራት ውስጥ ከዚህ በፊት የጥገኝነት ከለላ ጠይቀው ከሆ፣ ከNOAS ጋር በሚኖርዎት ውይይት ወቅት ይህን ጉዳይ ቢገልጹላቸው የበለጠ መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ።

5. ኖርዌይ ውስጥ የአንተን/የአንቺን የጥገኝነት ማመልከቻ የሚያየው ማን ነው?

የኖርዌይ የስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን፣ (UDI) የኖርዌይ መንግሥት አንድ አካል ነው። አንተን/አንቺን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ የመኖሪያ ፈቃድ እንደሚሰጥህ/እንደሚሰጥሽ ወይም እንደማይሰጥህ/እንደማይሰጥሽ ገምግሞ ይወስናል። UDI እያንዳንዱን የጥገኝነት ማመልከቻ በጥንቃቄ ገምግሞና ተመልክቶ የያንዳንዱን ሰው ጉዳይ በተናጠል ያስተናግዳል።

6. የጥገኝነት ከለላ ባቀረቡበት ወቅት ምን ሊከሰት ይችላል?

ጥገኝነትና ከለላ ጠያቂ ሆነው ከፖሊስ ዘንድ ሲመዘገቡ

- ፖሊስ ፎቶግራፍ ያነሳል የጣት አሻራዎትን ይመረምራል። በተጨማሪም ስለማንነትዎ፣ ወደ ኖርዌይም አመጣጥዎ በየት በኩል እንደነበረ ይጠይቅዎታል።
- ማንነትዎን የሚገልጽ ሰነድ ወይም ፓስፖርት ካለዎት በሚመዘገቡበት ወቅት ማቅረብ አስፈላጊ ነው።

ወደ ስደተኛ መጠለያ ማዕከል ይተላለፋሉ

- ከምዝገባ በኋላ ለአቅመ-አዳም ያልደረሱ ብቸኛ ወላጅ አልባ ስደተኞች መጠለያ ማዕከል ይወሰዳሉ። ለጥቂት ቀናትም በዚያ ቆይታ ያደርጋሉ።

- ከጥቂት ጊዜያት በኋላም ወደ አንድ ሌላ መጠለያ ማዕከል ይለወጣሉ።

- ከ16 ዓመት በታች ከሆንክና/ከሆንሽና፣ በኖርዌይ ውስጥ ከ3 ወራት በላይ ለመቆየት የምትችል/የምትችዪ ከሆነ፣ ትምህርት ቤት ገብቶ የመማር መብት እና ግዴታ አለብህ/አለብሽ። ሆኖም እድሜህ/እድሜሽ በ16 ዓመትና በ19 ዓመት መካከል ከሆነ፣ ትምህርት ቤት ገብቶ የመማር መብት ቢኖርህም/ቢኖርሽም ግዴታ ግን የለብህም/የለብሽም።

- አስቸጋሪ ይሆናል ብለው የሚያስቡት ነገር ካለ ከመጠለያው ማዕከል የስራ ባልደረቦች አባላት ጋር መነጋገሩ ጠቃሚ ነው። ምን እንደሚሉ ያዳምጡዎታል እንዲሁም ይረዱዎታል። የመጠለያው ማዕከል ሠራተኞች የቀን ተቀን እንክብካቤዎ ኃላፊነት አለባቸው።

የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ ይደረግልዎታል

- በመቀበያው ማዕከል በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናቶች ውስጥ፣ የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ ይደረግልዎታል። ይህ ለሁሉም ሰው ግዴታ ነው። የሳንባ ነቀርሳ ህመም ካለብዎት ህክምና ያገኛሉ።

- ሥር የሰደደ ደዌ ካለብዎትና እርዳታም የሚያስፈልግዎ ከሆነ፣ ለጤና ቢሮው የግድ ማሳወቅ አለብዎት።

ከNOAS መረጃ እና መምሪያ ይሰጥዎታል

- NOAS (ኖርዌይጂያዊ የጥገኝነት ጠያቂዎች ድርጅት) በደንብ በሚረዱት ቋንቋ አማካኝነት ስለጥገኝነት ሂደት የሚያስረዳ ፊልም ያሳይዎታል።

- ፊልሙን ከተመለከቱ በኋላ፣ ከNOAS ሰራተኞች አንዱ ከርስዎ ጋር ይነጋገራል። ውይይቱም እርስዎ በደንብ በሚረዱት ቋንቋ ይሆናል። ስለሚያመለክቱት የጥገኝነት ማመልከቻ ሂደት እና ስለመብትና ግዴታዎ መረጃ ይቀበላሉ። ጥገኝነት መጠየቅን፣ በተመለከተ ያለዎትን ጥያቄ ሁሉ በዚህ ውይይት ጊዜ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። ይህ ውይይት ለቀጣዩ የጥገኝነት ጥያቄ ቃለ-መጠይቅዎ እንዲዘጋጁ ይረዳዎታል።

- NOAS መንግሥታዊ ያልሆነ በሰብአዊነት መርሆ ላይ የተመሰረተ በኖርዌይ የጥገኝነት ከለላ ለሚጠይቁ ሰዎች መብት የሚሠራ ድርጅት ነው።

- የNOAS ሠራተኞች ምስጢር የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው። ይህም ማለት እርስዎ ለNOAS የሚናገሩት ነገር ሁሉ ለUDI፣ ለፖሊስ ወይም ለሌላ አካል ተላልፎ አይሰጥም። መሠረታዊ የጥገኝነት ከለላ ጥያቄዎትን፣ ማለትም ለምን የጥገኝነት ከለላ ለመጠየቅ እንደፈለጉ፣ ለመግለጽ መፍራት የለብዎትም።

ረዳት ሞግዚት ይመደብልዎታል

- ሞግዚቱ በእድሜ ጎልማሳ የሆነና መብትዎ በደንቡ መሰረት መጠበቁን የሚከታተል ሰው ነው። ሞግዚቱ ልክ ወላጆችዎ ከእርሶ ጋር ቢኖሩ ሊያደርጉልዎት የሚችሉትን ድጋፎች እንደነሱ ሆኖ ያደርግልዎታል።

- ከወላጆችዎ ወይም ከሌሎች ተንከባካቢ ሰዎች ጋር እስካልሆኑ ድረስ፣ እድሜዎ 18 ዓመት እስኪሞላዎት ድረስ ሞግዚት የማግኘት መብትዎ የተከበረ ነው።

- ረዳት ሞግዚቱ ለUDI አይሰራም።

- ከUDI ጋር በሚኖርዎት የጥገኝነት ቃለ-መጠይቅ ወቅት ረዳት ሞግዚቱ አብሮዎት ይሆናል።

- ወደ ሌላ የመጠለያ ማዕከል ከተቀየሩ፣ አዲስ ጊዜያዊ ሞግዚት ይመደብልዎታል።

ጠበቃ ይመደብልዎታል

- ጠበቃው የኖርዌይን ሕጎች ጠንቅቆ የሚያወቅ እና ለጥገኝነት ማመልከቻ ሊረዳዎት የሚችል ሰው ነው።

- በግልፅ እድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ከUDI ጋር የጥገኝነት ቃለ-መጠይቅ ከማድረጉ በፊት ነፃ የሕግ ድጋፍ ያገኛል። ሌሎች የዕድሜ ምርመራ ወይም የጥገኝነት ቃለ-መጠይቅ ካደረጉ በኋላ ጠበቃ ይመደብላቸዋል።

በUDI ቃለ-መጠይቅ ይደረግልዎታል

- የጥገኝነት ከለላ ጥያቄ ባቀረቡበት ወቅት የሚኖረው የቃለ መጠይቅ ወቅት ጥያቄዎትን በደንብ እንዲያብራ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ስለሆነ ከUDI ጋር በሚኖርዎት የቃለ-መጠይቅ ወቅት ዋናው በደንብ ማብራራት ያለብዎት አቢይ ጉዳይ፣ ወደ ትውልድ አገርዎ ቢመለሱ ምን ሊደርስብዎት እንደሚችል፣ በተጨባጭና በዝርዝር ስለዚህ ጉዳይ አስረግጠው መናገር ይጠበቅብዎታል።

- በቃለመጠይቅህ ጊዜ ስለ ማንነትህና ስለ ቤተሰብህ እንዲሁም ወደ ኖርወይ ስላደረግከው ጉዞ መናገር አለብህ፡፡

- ከUDI ጋር በሚኖርዎት የቃለ-መጠይቅ ወቅት ረዳት ሞግዚትዎ እና አስተርጓሚዎ አብሮዎት ይሆናሉ።

- በቃለ-መጠይቁ ወቅት በቃለ መጠይቅ አድራጊውና በእርስዎ መካከል የሚደረገውን ቃለ-ምልልስ አስተርጓሚው ከመተርጎም ሌላ ምንም ማድረግ አይችልም። እንዲሁም በቃለ-መጠይቁ ጊዜያት ያየውን ወይም የሰማውን ነገር ለሌሎች እንዲናገር አይፈቀድለትም።

የዕድሜ ምርመራ

- የጥገኝነት ከለላ በኖርዌይ ውስጥ በሚጠይቁበት ወቅት እድሜዎ እጅግ አስፈላጊ ነው። እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ አመልካቾች ለአቅመ-አዳም እንዳልደረሱ ስለሚቆጠር፣ ከአዋቂዎች የበለጠ በጣም ሰፊ መብቶች ይኖራቸዋል።

- የጥገኝነት ከለላ የጠየቁ ልጆች ከአዋቂዎች በላይ ከፍተኛ እንክብካቤ ስለሚደረግላቸው፣ አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ አዋቂዎች ከ18 ዓመት በታች ነን ይላሉ። ሌሎች የጥገኝነት ከለላ የሚጠይቁ ሰዎች ደግሞ ትክክለኛ እድሜያቸውን በደንብ አያውቁትም። ስለሆነም UDI እድሜያቸው ከ15 እስከ 18 ዓመት መካከል ነው የሚሉትን የእድሜ ምርመራ እንዲያደርጉ ይጠይቃል።

- የዕድሜ ምርመራ በግምት ምን ያህል ዕድሜ ክልል ውስጥ እንደሆኑ የሚያሳይ የህክምና ምርመራ ነው። እነዚህ ምርመራዎች ምን ምን እንደሚያካትቱ የበለጠ መረጃ ያገኛሉ።

- UDI ዕድሜዎትን ለመወሰን ሊረዱ የሚችሉ ሌሎች ነገሮችን እንደ መታወቂያ ወረቀቶች፣ ምስክር ወረቀቶች እና ከሌሎች አገራት የተገኙ መረጃዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባል። ስለ ዕድሜዎ እና ማንነትዎ ሁለቱንም በተመለከተ ማናቸውንም ግልፅ ለማድረግ በሚደርገው ጥረት ለመርዳት ሙከራ ቢያደርጉ ጠቃሚ ነው።

- የእድሜ ምርመራ በበጎ ፈቃደኝነት ላይ ይደረጋል። መመርመር ካልፈለጉ፣ እንደ አዋቂ ሊቆጠሩ ይችላሉ። ይህም ለምታቀርቡት የጥገኝነት ማመልከቻ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል።

- ሆን ብለው ትክክለኛ ያልሆነ ዕድሜ ከተናገሩና እና UDI በኖርዌይ ውስጥ ከለላ ወይም ጥበቃ አያስፈልግዎትም ብሎ ካለ፣ ከአገር ሊባረሩ ይችላሉ። ከአገር መባረር ማለት ለወደፊቱ ወደ ኖርዌይ ወይም ሌሎች የአውሮፓ አገራት ተመልሰው እንዳይገቡ ይዳርጋል።

- UDI ዕድሜዎ ከ18 ዓመት በላይ እንደሆነ ከወሰነ፣ ረዳት ሞግዚት ወይም ጠበቃ አያገኙም። ማመልከቻዎት ውድቅ ከሆነ ግን ጠበቃ ይመደብልዎታል።

መልስ ከUDI ያገኛሉ

የመኖሪያ ፈቃድ ወይም አሉታዊ መልስ

በኖርዌይ ውስጥ ለመኖር ተፈቅዶልዎት ከሆነ ወይም ደግሞ ካልተፈቀደልዎ ጠበቃዎት ይነግርዎታል።

የመኖሪያ ፈቃድ ከተሰጠዎት፣ በአንድ ኮምዩን ወይም አጥቢያ እንዲኖሩ ይደረጋል

- በዚህ ጉዳይ ላይ በመጠለያ ማዕከል ውስጥ ከሚገኙ የስራ ባልደረቦች የበለጠ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

የተገደበ የመኖሪያ ፈቃድ ከተሰጠዎ፣ ወደ ሌላ የመጠለያ ማዕከል ሊላኩ ይችላሉ።

- ስለዚህ የመኖሪያ ፈቃድ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላሉ። በዚህ ጉዳይ ላይም ጠበቃዎት ሊረዳዎት ይችላል።
- በዚህ ጉዳይ ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት የመጠለያ ማዕከሉን ሠራተኞች ያነጋግሩ።

ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ ይግባኝ ማለት ይችላሉ

- እንደ ደንቡ፣ ይግባኝዎ እየታየ መልስ በሚጠባበቁበት ወቅት ኖርዌይ ውስጥ ሊቆዩ ይችላሉ።
- የኖርዌይ መንግሥት ይግባኝዎትን እንደገና እንዲመለከተልዎ ጠበቃዎት የይግባኝ ደብዳቤ ማመልከቻ በመጻፍ ሊረዳዎት ይችላል።

ይግባኝዎ እንዲሁ ውድቅ ከተደረ፣ ወደ ትውልድ አገርዎ መመለስ አለብዎት

- **በአለም አቀፍ የስደተኛ ጉዳዮች ድርጅት (IOM) ወደ አገርዎ ለሚያደርጉት ጉዞ እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ። IOM የጉዞ ወጪዎችን ሊሸፍን እና የጉዞ ሰነዶችን እንዲያገኙ ሊረዳዎት ይችላል።**
- በመጠለያ ማዕከሉ ከሚገኙ ሠራተኞች ስለመልስ ጉዞዎ የበለጠ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

ወደ ትውልድ አገርዎ ለመመለስ ከፈለጉ፣ በዚህ ሁኔታ ዕርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ።

- ወደ አገርዎ ለመመለስ እርዳታ ከፈለጉ ከUDI መልስ በፊትም ሆነ የጥገኝነት ጉዳይዎት እየታየ ባለበትም ወቅት ወይም አሉታዊ የድጋሚ መልስ ከተሰጥዎ በኋላ ወደ አገርዎ ለመመለስ ዕርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ።
- ረዳት ሞግዚቷ/ ሞግዚትዎ በዚህ ውሳኔ እንዲሁ መስማማት አለባቸው።
- በመመለስ ጉዞዎ ጊዜ IOM ነው የሚረዳዎት። IOM የጉዞ ወጪዎትን ሊሸፍን እና የጉዞ ሰነዶችን እንድታገኙ ሊረዳዎት ይችላል።
- በበጎ ፈቃደኝነት ወደ ትውልድ አገርዎ ለመመለስ ከፈለጉ በIOM እርዳታ የገንዘብ ስጦታ ሊድረግልዎት ይችላል። የኖርዌይ መንግሥት ከአንዳንድ የተወሰኑ አገራት ጋር የመልሶ ማቋቋምያ ፕሮግራሞች አሉት። በትውልድ አገርዎ ውስጥ ይህ ፕሮግራም ካለ፣ ወደ አገርዎ በምትመለሱበት ጊዜ ይህንን የገንዘብ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ። .
- ይህንን ጉዳይ በመጠለያ ማዕከሉ ከሚገኙ ሠራተኞች ጋር በመወያየት ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

ለጥገኝነት ጠያቂዎች ጠቃሚ ምክሮች

- በዝርዝርና በተጨባጭ ለምን የትውልድ መንደራችሁን ለቃችሁ እንድትወጡ እንደተገደዳችሁ እንዲሁም ወደ አገራችሁ ብትመለሱ ምን እንደሚጠብቃችሁ በደንብ አስረግጣችሁ መናገር አለባችሁ።
- የግድ ወደ አገርዎ መመለስ ካለብዎት በደረሰብዎት ነገር ላይ እና ሊደርስብዎ በሚችለው ነገር ላይ ያትኩሩ።
- እድሜህን ለሚመለከቱ ጥያቄዎች ዝርዝርና ውሱን የሆኑ መልሶችን ስጥ፡፡

- በዝርዝርና በወጉ ስለ አድሜዎ የተጠየቁትን ይመልሱ ።
- ከእርስዎ ጋር ልጆች ካሉ ስላሉበት ሁኔታ እና ቀደም ሲል ስለደረሰባቸው ነገር ይግለፁላቸው።
- ያልተረዱት ነገር ካለ ቃለ-መጠይቅ አድራጊውን ይጠይቁት።
- ለጥገኝነት ማመልከቻዎ ይረዱኛል ብለው ያያያዝዋቸው አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ካለዎት እነዚህን ሰነዶች ቃለ-መጠይቅ በሚደረግልዎት ጊዜ ይዘው ይሂዱ።
- እውነቱን ይናገሩ። እውነት ያልሆነ ነገር ከተናገሩ፣ የጥገኝነት ጥያቄዎ ውድቅ እንዲሆን ሊዳርግዎት ይችላል። በተጨማሪም ከኖርዌይ ለቀው እንዲወጡ ሊደረጉ ይችላሉ። ይህም ወደፊት ወደ ኖርዌይ እና ወደ አብዛኛዎቹ ሌሎች የአውሮፓ አገራት እንዳይገቡ ሊያደርግዎት ይችላል።

እንደ ጥገኛ ጠያቂነትዎ ሊኖርዎት የሚችሉ መብትና ግዴታዎ

ስለማንነትዎ ለመግለጽ የመተባበር ግዴታ አለብዎት

የኖርዌይ መንግሥት ስለማንነትዎና፣ እድሜዎ ስንት እንደሆነ ማወቅ እጅግ አስፈላጊው ነው። ስለሆነም ማንነትዎትን የሚያሳይ ማስረጃ ቢያቀርቡ እጅግ ይጠቅማል። የትውልድ አገርዎት መንግሥት ክትትል የሚያደርግብዎት ከሆነ የኖርዌይ መንግሥት የመታወቂያ ሰነዶችን ለማግኘት ሲሉ እነርሱን እንድትገናኙ አያስገድድዎትም።

የኖርዌይ መንግሥት ስለማንነትዎ ጥርጣሬ ካደረበት፣ የሚከተሉት አሳሳቢ ጉዳዮች ሊያጋጥምዎት ይችላል፡-

- ያለመታመን
- የመኖሪያ ፈቃድ የማግኘት እድልዎ መጥበብ
- ሊያገኙዋቸው የሚችሉ ሙብቶችን ማጣት
- የተገደበ የመኖሪያ ፈቃድ ማግኘት

ትክክለኛ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለብዎት

እንደ ጥገኝነት ጠያቂ ለምን ጥገኝነትና ከለላ እንደሚጠይቁ ማብራራት ይኖርብዎታል። ስለሆነም በተቻለዎት መጠን ለመተባበር እና አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ለማቅረብ የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ ይኖርብዎታል።

የጥገኝነት ከለላ ለማግኘት ከማመልከትዎ በፊት የሰሟቸውን ነገሮች ሁሉ ወደ ጎን በመተው ለኖርዌይ ባለስልጣናት ለጥገኝነት ጥያቄዎት ትክክለኛውን የእርስዎን ማንነት የሚመለከት መረጃ መስጠት እና መግለጽም አስፈላጊ ነው። ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ መስጠት ያስቀጣል። ከሃገር እስከማባረርም ሊያደርስ ይችላል።

የጥገኝነት ከለላ ጠይቀው መልስ እየጠበቁ ባሉበት ወቅት የመስራት ሙብት ሊኖርዎት ይችላል፥

የጥገኝነት ማመልከቻዎ እየታየ ባለበት ወቅት ማንነትዎን በተመለከተ በቂ መረጃና ፓስፖርት ማቅረብ ከቻሉ ሥራ የመሥራት ሙብትዎ የተጠበቀ ነው። ረዳት ሞግዚትዎ ሥራዎት ከትምህርት ከፍለ-ጊዜው ጋር የማይጋጭ መሆኑን መስማማት አለባቸው።

ህክምና የማግኘት መብት አለዎት፣
የጥገኝነት ማመልከቻዎ እየታየ ባለበት ወቅት የሚያስፈልግዎትን ሕክምና የማግኘት መብት ይኖርዎታል። በኖርዌይ ውስጥ እድሜው ከ16 ዓመት በላይ የሆነው ማንኛውም ሰው አብዛኛውን ጊዜ ለሚደረግለት ሕክምና የግል ድርሻ ክፍያ መክፈል አለበት። የሥነ-አእምሮ ሃኪም ድጋፍ የሚፈልጉ ከሆነ ወጪዎችን UDI ይሸፍናል። ለተጨማሪ መረጃ የመጠለያ ማዕከሉን ሠራተኞች ያነጋግሩ። ከፍተኛ የሆነ የጤና ችግሮች ካለብዎት ለUDI እና ለረዳት ሞግዚትዎ የማሳወቅ ግዴታ አለብዎት።

የጥገኝነት ማመልከቻዎትን ማንሳት ይችላሉ ፣
የጥገኝነት ማመልከቻዎ መታየቱን እንዲያቆም በማናቸውም ጊዜ ማድረግ ይችላሉ። ከዚህ በኋላም ወደ ትውልድ አገርዎ ለመመለስ ለዓለም አቀፍ የስደተኛ ጉዳይ ማዕከል IOM ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላል።

ወላጆችዎትን ወይም ዘመዶችዎን እንዲፈለጉልዎት እርዳታ ይፈልጋሉ?
ወላጆችዎን ወይም ሌሎች ዘመዶችዎትን ለመገናኘት ወይም ለማግኘት እርዳታ ከፈለጉ መጠለያ ማዕከሉ ውስጥ የሚገኙትን ሠራተኞች ያነጋግሩ።

ቀይ መስቀል ቤተሰቦችዎትን እንዲያገኙ ሊረዳዎት ይችላል።

ምስጢር የመጠበቅ ግዴታ

ፖሊስ፣ UDI፣ UNE ምስጢር የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው። ይህም ማለት የጥገኝነት ማመልከቻዎትን በተመለከተ ለትውልድ አገርዎ መንግሥት መረጃ መስጠት አይችሉም ማለት ነው። በእርስዎ የጥገኝነት ማመልከቻ ላይ ለማይሳተፉ ሰዎች እርስዎ ስለተናገሯቸው ነገሮች ምንም ነገር መናገር አይችሉም። ምስጢር የመጠበቅ ግዴታን አለመወጣት ያስቀጣል። ስለሆነም ጥቢቃና ከለላ ስለጠየቁበት ሁኔታ ሳይፈሩ በዝርዝር መግለጽ መቻል አለብዎት።

አስተርጓሚው፣ ጠበቃው፣ ጤና ባለሙያዎች እና NOAS ጭምር ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው። ይህም ማለት እርስዎ የተናገሩትን ማናቸውንም ነገሮች አሳልፈው ማውራት፣ ለUDI፣ UNE፣ ለፖሊስ ጭምር አሳልፈው መናገር አይችሉም።

አድራሻዎች

የኢሚግሬሽን ፖሊስ ክፍል (POLITIETS UTLENDINGSENHET)
ፖሊስ አዲስ የገቡ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ይመዘግባል።
አንድ ጊዜ የጥገኝነት ማመልከቻቸው ኣሉታዊ መልስ ካገኘ በኋላ በፈቃዳቸው ከኖርወይይ ያልወጡ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ያስወጣል።

የፖስታ አድራሻ: Postboks 8102 Dep., NO-0032 Oslo, Norway
የመጠየቂያ አድራሻ: Christian Krohgs gate 32, Oslo
ስልክ.: +47 22 34 24 00, ፋክስ: +47 22 34 24 80
ኢ-ሜይል: pu@politiet.no

የኖርወይይ የኢሚግሬሽን ጉዳይ ዳይሮክቶሬት /UDI/
ግዴታዎቹ የጥገኝነት ማመልከቻዎችን፣ ቪዛ እና የዜግነት ጉዳዮችን ማየትን እና ቤተሰቦችን መልሶ ማገናኘትን የሚያካትት መንግስታዊ ተቋም ነው። ከዚህ በተጨማሪ UDI ለቅበላ ማዕከላቱ ኃላፊነት አለበት።

የፖስታ አድራሻ: Postboks 8108 Dep., NO-0032 Oslo, Norway
የመጠየቂያ አድራሻ: Hausmannsgt. 21, 0182 Oslo
ስልክ.: +47 23 35 15 00, ፋክስ: +47 23 35 15 01
ድረ-ገፅ: www.udi.no, ኢ-ሜይል: ots@udi.no

ዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት /IOM/
በፈቃደኝነት ድጋፍ አግኝቶ መመለስን በተመለከተ የቀረበ መረጃ

የፖስታ አድራሻ: Postboks 8927 Youngstorget, NO-0028 Oslo, Norway
የመጠየቂያ አድራሻ: Storgata 10a, ሁለተኛ ፎቅ, Oslo
ስልክ.: +47 23 10 53 20, ፋክስ: +47 23 10 53 21
ኢ-ሜይል: osloreturn@iom.int

የስራ ሰዓታት: በስራ ቀናት: 10:00 – 15:00, ቅዳሜ እና እሁድ: ዝግ ነው

የኖርወይ የስደተኞች ይግባይ ቦርድ (UTLENDINGSNEMNDA – UNE)፤
የተወሰኑ ተቀባይነትን ያጡ ማመልከቻዎች ጋር በተያያዙ የሚቀርቡ ይግባኞችን የሚያይ ከፊል የዳኝነት አስተዳደር አካል ነው።

የፖስታ አድራሻ: Postboks 8165 Dep., NO-0034 Oslo, Norway
የመጠየቂያ አድራሻ: Stenersgt. 1B/C, 0050 Oslo
ስልክ.: +47 21 08 50 00, ፋክስ: +47 21 08 50 01
ድረ ገፅ: www.une.no, ኢ-ሜይል: postmottak@une.no

የኖርወይ ቀይ መስቀል (NORGES RØDE KORS)
በቤተሰብ አባላት መካከል በጦርነት፣ በግጭት ወይም በአደጋ ምክንያት መለያየት ሲከሰት መልሰው እንዲገናኙ ግንኙነቶችን የሚያመቻች እና አገልግሎቶችን የሚሰጥ ድርጅት ነው። ቀይ መስቀል ለUDI ወይም ለሌሎች እርስዎን በተመለከተ መረጃ አይሰጥም። የሚሰጠው አገልግሎትም ነፃ ነው።

የፖስታ አድራሻ: Postboks 1 Grønland, NO-0133 Oslo, Norway
የመጠየቂያ አድራሻ: Hausmannsgt. 7, 0186 Oslo
ስልክ.: +47 22 05 40 00
ድረ ገፅ: www.rodekors.no, ኢ-ሜይል: tracing@redcross.no

NOAS መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብአዊ መብት ድርጅት ሲሆን፣ሥራውም መረጃንና የህግ እርዳታን ጥገኝነትና ከለላን ለሚጠይቁ ሰዎች መስጠት ነው። እንዲረዳ ሆኖ የተቋቋመ ድርጅት ነው።

ይህ ጥራዝ ለርስዎ በኖርዌ ውስጥ ጥገኝነትንና ከለላን ለሚፈልጉ ሰው ጠቃሚ መረጃዎችን እንዲያካትት ተደርጎ የተዘጋጀ ነው።

ኖርወጂያዊ ድርጅት ለጥገኝነት ጠያቂዎች (NOAS)
የጉብኝት አድራሻ: Torggata 22, Oslo, Norway
የፖስታ አድራሻ: P.O.Box 8893 Youngstorget, NO-0028 Oslo, Norway
ስልክ: +47 22 36 56 60, ፋክስ: +47 22 36 56 61
ድህረ ገጽ: www.noas.org, ኢ-ሜይል: noas@noas.org